ICARDA

Science for resilient livelihoods in dry areas

በግ ማደለብ፡ ለአርሶ አደሮችና ለግብርና ኤክስቴንሽን ሙያተኞች የተዘጋጀ የስልጠና ማኑዋል

ጄን ዋማቱ፣ ሙሉቀን ዘለቀ፣ ተስፋዬ አቢሶ፣ተስፋ ጌታቸው እና ናሆም ኤፍሬም



ታህሳስ 2015 ዓ.ም

ማኑዋል እና መመሪያዎች

ICARDA ማኑዋልና መመሪያዎች ተከታታይ ክፍሎች የማዕከሉን ጠቅለል ያለ ምክር እና ተመራማሪዎች የግብርና ምርታማነትን ከፍ ለማድረግና ትሮፒካል ባለሆኑ ደረቅ አካባቢዎች ውስጥ የሚገኙ በገጠራማው ክልል የሚኖሩ ማህበረሰቦች ላይ የሚደርሱ ከፍተኛ ተግዳሮቶችን ለመርታት የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ለማቅረብ ያለውን ልምድ የሚያነሱ ናቸው።።

እንደ ሃሳብ የቀረቡ ምንጮች

ጄን ዋማቱ፣ሙሉቀን ዘለቀ፣ተስፋዬ አቢሶ እና ናሆም ኤፍሬም 2021። የበግ ማደለብ፣ ለአርሶ አደሮችና የግብርና ኤክስቴንሽን ሰራተኞች የተዘጋጀ የስልጠና ማኑዋል። አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፣ አለም አቀፉ የደረቃማ አካባቢዎች የግብርና ምርምር ማእከል (ICARDA)
የሽፋን ፎቶ፣ ሙሉቀን ዘለቀ

ስለ CGIAR

CGIAR የወደፊትን የምግብ ዋስትና በተመለከተ የምርመር ስራ የሚያከናውኑ ድርጅቶችን ግንባር የሚፈጥር አለም አቀፍ አጋርነት ነው።። የ CGIAR የቁም እንስሳት ላይ የሚከናወን የምርምር ፕሮግራም በአነስተኛ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ አርሶ አደሮችን፣ አርብቶ አደሮችን እና አርሶ/አርብቶ አደሮችን ወደ ዘላቂ፣ ደረጃው ከፍተኛ ወደሆነ የአኗኗር ዘይቤ እንዲሸጋገሩና የወደፊት ትውልድን ለመመገብ ድጋፍ ለሚያደርጉ ምርታማ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ ለማድረግ ምርምር ተኮር የሆኑ የመፍትሄ ሃሳቦችን ያቀርባል።። ምርታማነትን እና የቁም እንስሳ የግብርና-ምግብ ስርአቱን በዘላቂ መንገድ ትርፋማ ለማድረግ ያለመ ሲሆን ይህውም ስጋ፣ ወተትና እንቁላልን በከፍተኛ መጠን በማቅረብ እንዲሁም በማደግ ላይ ያሉት አገራዎች ውስጥ በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ ትርፋማነትና ምርታማነትን ለማሳደግ ያለመ ነው።። ፕሮግራሙ በአንድ ላይ 5 ቁልፍ አጋሮችን ግንባር እንዲፈጥሩ አድርጓል እነዚህም አለም አቀፉ የቁም እንስሳት ተቋም (ILRI) በቁም እንስሳት ላይ ልዩ ተልእኮ ይዞ የተነሳ ተቋም ሲሆን እንዲሁም በመናዎች ላይ የሚሰራው አለም አቀፉ የትሮፒካል ግብርና ማእከል (CIAT)፣ በአነስተኛ እና ደረቅ መሬት ስርአት ላይ የሚሰራው አለም አቀፉ የደረቅ አካባቢዎች ምርምር ማእከል (ICARDA)፣ በተለይም በእንስሳት ጤና እና በዘረመል ላይ ልዩ ልምድ ያለው የስውዲሽ የግብርና ሳይንስ ዩኒቨርስቲ (SLU) እና ምርምርን ከልማትና የፈጠራ ስራ እንዲሁም ደረጃ ወደማሳደግ ሂደት ጋር የሚያገናኘው ደች ጌሴልሻፍት ፉር ኢንተርናሽናል ዙሳሜናርቤት (GIZ) ናቸው።።

ስለ ICARDA

በ1977 አውሮፓ አቆጣጠር የተቋቋመው የደረቃማ አካባቢዎች አለም አቀፍ የግብርና ምርምር ማእከል (ICARDA) ለትርፍ ያልተቋቋመ ተቋም ሲሆን CGIAR የምርምር ማዕከል በማደግ ላይ ባሉ አገራት ትሮፒካል ባልሆኑ ደረቃማ አካባቢዎች ዘላቂ የግብርና ልማትን እውን ለማድረግ የፈጠራ ሃሳብ የታከለባቸውን የመፍትሄ ሀሳቦች በማቅረቡ ላይ የሚያተኩር ተቋም ነው።።
እኛ የምናቀርበው የፈጠራ ስራ የታከለባቸውን፣ ሳይንስ ተኮር የሆኑ እና አኗኗርን የሚያሻሽሉ እና በድህነት አረንቋ ውስጥ የሚገኙ አነስተኛ አርሶ አደሮችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የሚረዳ መፍትሄ ነው።። ይህንንም የምናከናውነው ምርምርን ከልማት እና ከአቅም ማጎልበት ጋር በማቆራኘት በሚከናወን ስትራቴጂክ አጋርነት እንዲሁም የጾታ እኩልነትን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባትና ትሮፒካል ያልሆኑ ደረቃማ አካባቢዎችን በመለወጡ ረገድ የወጣቶችን ሚና ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው።።

አድራሻ

ዳሊያ ህንጻ፣ 2ኛ ፎቅ፣ በሸር ኤል ቃስር ጎዳና፣ ቬርደን፣ ቤሩት፣ ሊባኖስ 1108-2010
www.icarda.org

ምስጋና

ይሄ ስራ በICARDA አማካኝነት የኢትየጵያው ስማርት (SmaRT) ፕሮጀክት አካል በመሆን እና በCGIAR የትብብር የምርምር ፕሮግራም (CRP)፣ የቁም እንስሳት የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወን ነው።። ለቦንጋ የግብርና ምርምር ማዕከል፣ ለአረካ የግብርና ምርምር ማዕከል እና ለደብረብርሃን የግብርና ምርምር ማዕከል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ልባዊ ምስጋናችንን ለማቅረብ እንወዳለን።።

መሻርያ

ይህ ሰነድ በክሬቲቭ ኮመንስ አትሪቢዮሽን-ሼርአላይክ 4.0 አለም አቀፍ ፍቃድ መሰረት ጥቅም ላይ እንዲውልን ፍቃድ ተሰጥቶበታል።። የዚህን ፈቃድ ግልባጭ ለመመልከት http://creativecommons.org/licenses/by-sa/4.0/ ይጎብኙ
በሌላ መልኩ ማስታወሻ እስካልቀረበበት የዚህን ህትመት ማንኛውንም ክፍል ወይም የተወሰነ ክፍል በግልባጭ መውሰድ፣ ማባዛት ወይም ማተምና ማሰራጨት፣ ማሳየት ወይም ማስተላለፍ ያለ ምንም ፍቃድ ይቻላል እና ቀጥሎ በተመለከቱት ሁኔታዎች የትርጉም ስራ ማከናወን፣ እንደሁኔታው የማመቻቸት ወይም ሌሎች የተወሰነ ክፍልን የመውሰድ ስራ ማከናወን ይቻላል።።

መውሰድ፡ ስራው በአሳታሚው ወይም በደራሲው ፈቃድ እንዲሰጥበት ሃሳብ እስከሌለ ድረስ መወሰድ ይችላል።።.
ማጋራት፡ ይህ ስራ ከተለወጠ፣ ከተቀየረ ወይም ወደ ሌላ ስራ ከተጨመረ በውጤቱ የሚመጣው ስራ ከዚህ ጋር ተመሳሳይ ወይም አንድ አይነት በሆነው ፍቃድ ብቻ መሰራጨት ይኖርበታል።።

CGIAR
A CGIAR Research Center
cgiar.org

ማውጫ

መግቢያ 3
ክፍል 1፡ በበግ ማደለብ መጀመር 4
ክፍል 2፡ የሚደልበውን በግ መምረጥ 8
ክፍል 3፡ በማደለብ ሂደት በጎችን መንከባከብ 10
ክፍል 4፡ በጎችን ለማደለብ መመገብ እና የአመጋገባቸው ሁኔታ 15
ምእራፍ 1፡ የሚደልቡ በጎች የመኖ ፍላጎት 15
ምእራፍ 2፡ የመኖ አይነቶች 19
ምእራፍ 3፡ የራሽን ማመዛዘን 26
ክፍል 5፡ ንግድን መሠረት ያደረገ የበግ ድለባ 30
ተጨማሪ ንባብ 38

1. መግቢያ

በግ ማደለ በኢትዮጵያ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ሲተገበር የቆየ ተግባር ሲሆን በተለይም ፍላጎት በሚኖርባቸው የበዓላት ወቅቶች በእጅጉ ይተገበራል። ምንም አይነት ጉዳት የሌለውና ዳልጋ እንስሳቶችን ከመንከባከብ ይልቅ ትርፋማ ነው። ባህላዊው የበጎች ማደለብ ኡደት **6** ወራት ወይም ከዚያ በላይ ሊፈጅ ይችላል። አርሶ አደሮች በቂ እና ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያለው መኖ ባለማግኘታቸው፣ በእውቀት እና የተሻሻለ የማደለቢያ ስርአትን የተመለከቱ ክህሎቶች ባለመከተላቸው እና ተጓዳኝ መኖ ምገባ ዘዴዎችን የሚጠቀሙ ባለመሆናቸው የማደለበያ ጊዜ ይጨምራል። ስለሆነም በአነስተኛ እንስሳት እሴት ሰንሰለት መኖ እና አመጋገብን ማሻሻል የአለም አቀፉ የደረቃማ አካባቢዎች የግብርና ምርምር ማእከል፣ ICARDA የትኩረት አቅጣጫዎች ናቸው። ትኩረት የሚሰጠው የተሻሻለ እና ንግድ ተኮር በግ ማደለብ ላይ ሲሆን በመለስተኛ ስርአት በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ሙክቶችን በከፊል የአካባቢው በሚገኙ የመኖ ምንጮች ከመሸጣቸው በፊት መመገብ ያተኮሩ መረጃዎችን የያዘ ነው።

ይሄ ማኑዋል ቀላል እና በሂደት የተሞከሩ የበግ ማደለብ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚገኙ አርሶ አደሮች እና የኤክስቴንሽን ሰራተኞች ተግባራዊ መመሪያ ነው። በመኖ እና በመኖ አያያዝ በአነስተኛ ደረጃ አምራቾች እና የኤክስቴንሽን ሰራተኞች ተግባራዊ ሊደረግ በሚችሉ አማራጮች ላይ የሚያጠነጥኑ መረጃዎችን የያዘ ነው።



ክፍል ፣፡ በጎችን በማደለብ መጀመር

የክፍሉ አላማ

ይህ ክፍል አላማውን ያደረገው በበግ ማደለብ ስራ ላይ ለተሰማሩ ስለ በግ ማደለብ እና አስፈላጊነቱ መግቢያ የሚሆናቸውን መረጃ መስጠት ላይ ነው። በዚህ ክፍለ ጊዜ ውስጥ ሰልጣኞች ስለ በግ ማደለብ ጽንሰ ሃሳብ፣ ገጽታዎች እና አስፈላጊነቱ መረጃ ይደርሳቸዋል።

ከዚህ የመማማር ክፍለ ጊዜ በኋላ ሰልጣኞች የሚከተለውን ማድረግ ይችላሉ

- ✓ስለ በግ ማደለብ ትርጉም መስጠት
- ✓ለአነስተኛ የአኗኗር ደረጃ ስለ በግ ማደለብ አስፈላጊነት ውሳኔ መስጠት

ከግምገማ በፊትና በኋላ ጥያቄዎች:

- ✓ የበግ ማደለብ ቁልፍ ገጽታዎች ምንድን ናቸው?
- ✓ በግ ማደለብ ሌሎች የቁም እንስሳቶችን ከማደለብ ጋር ሲነጻጸር ምን ይመስላል?

የበግ ማደለብ ምንድን ነው?

በግ ማደለብ የታሰበው የስጋ መደለብ እና የጥራት ደረጃን እውን ለማድረግ ፈጣን እድገት እና የስብ ክምችትን ለማነቃቃት የንጥረ ነገር ይዘታቸው



ክፍል ፣፡ በጎችን በማደለብ መጀመር

ከፍተኛ የሆኑ መኖዎችን መመገብ እንደሆነ ይገለጻል። የበግ ማደለብ ፕሮግራም አላማውን ያደረገው ከፍተኛ የእድገት ደረጃን መቀዳጀት እና በአጭር ጊዜ ውስጥ (75-90 ቀናት) የሚፈለገውን የስጋ ውጤት ማግኘት ላይ እና በእያንዳንዱ ግብአት ልክ ምርታማነትን መጨመር ላይ ነው። የበግ ማደለብ ዝቅተኛ የኢንቨስትመንት ወጪ ያለው ሲሆን የዳልጋ እንስሳቶችን ከማርባት ጋር ሲነጻጸር ትርፉ እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ተረጋግጧል እንዲሁም ከፍተኛ እና ፈጣን የኢኮኖሚ ውጤት ያለው በመሆኑ ስራው በፍጥነት እንዲያድግ የሚረዳ ነው።



ክፍል 2፡ የሚደልቡ በጎችን መምረጥ

የክፍሉ አላማ

በማደለብ ኡደት በጎችን መምረጥ ምርታማነትን እና የተሻለ ትርፍን እውን ለማድረግ አስፈላጊ ነው። በዚህ ክፍል ሰልጣኞች በጎችን በሚመርጡበት ጊዜ ሊጠቀሙባቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች ላይ እውቀትና ክህሎት ይሰጣቸዋል።

ከዚህ ክፍለ ጊዜ በኋላ ሰልጣኞች

- ✓ የድልብ በጎች ምርጫ አሰፈላጊነትን ይረዳሉ
- ✓ የሚደልቡ በጎችን ሲመርጡ የሚፈልጉትን ባህርይ መለየት ይችላሉ።
- ✓ በበጎቹ እድሜ ልየታ ላይ እውቀቱ ይኖራቸዋል

የምዘና በፊትና በኋላ ጥያቄዎች:

1. በጎችን ለማደለብ ምርጫ ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው?

2. የሚደልቡ በጎችን ለመምረጥ ጥቅም ላይ የሚውሉት መስፈርቶች የትኞቹ ናቸው?

3. የበጎቹን እድሜ እንዴት መወሰን ይችላሉ?

ዕድሜ፡

ለመደለብ የሚችሉበት የዕድሜ ክልል ላይ የሚገኙ በጎችን መምረጥ፡ ኢትዮጵያ ውስጥ በዝርያ መለያየት ምክንያት የሚደልቡ በጎች እድሜ ተመሳሳይ አይደለም። ይሁን እና የገበያውን ፍላጎት ለማርካት የሚደልቡ በጎች በዝርያቸው ላይ በመመርኮዝ በ9 እና 12 ወራቶች መካከል ላይ የእንዲሆኑ ይመከራል። በዚህ እድሜ የክብደት መጨመር አቅማቸው እና የመኖ ቅየራ ብቃት እጅግ ከፍተኛ ነው። በእድሜ ከፍ ያሉ እንስሳቶች የዕለት የክብደት ጭመራ እና የመኖ ቅየራ ብቃት እጅ ዝቅተኛ በመሆኑ የማደለብ ሂደቱን ወጪ ከፍተኛ ያደርጉታል። የበጎች የጥርስ አቋም እድሜያቸውን በጥሩ ሁኔታ የሚጠቁም ነው

(ምስል 1)

የጤና ሁኔታ፡

የድልብ በግ ሲገዛ እንስሳቶቹን ባህሪያቸውን ለማጤን ሳንረብሻቸው ልንቀርባቸው ይገባል። ይህውም እረፍት አልባነት፣ ንቃት፣ ሃይለኝነት፣ መንቀጥቀጥ፣ የአተነፋፈስ ሁኔታ (መደበኛ ወይም ጫና ያለበት)፣ እና መደበኛ እንቅስቃሴ ናቸው። የአፍንጫ የቅርብ ግምገማ፣ የፈሳሽ ሁኔታን በመመልከት)፣ አፍ (መጥፎ ጠረንን፣ ያልተለመደ ፈሳሽን፣ በከንፈር፣ በድድ፣ በምላስ ዙሪያ የሚገኙ ቁስሎችን ለመመልከት)፣ እና አይኖችን (ፈሳሽ መኖሩን ለመመልከት) በቅርበት መመርመር

ክፍል 2፡ የሚደልቡ በጎችን መምረጥ



8 ወር




1.5 ዓመት



2 ወር



3 ወር




4 ዓመት

ክፍል 2፡ የሚደልቡ በጎችን መምረጥ

ቆዳው ላይ እብጠት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ መመርምር ይኖርበታል።ጤናቸው የተጎዱ እና በህመም ያሉ በጎች ወይም በመኖ እጠረት ምክንያት እድገታቸው የተገደቡ በጎች በንጽጽር ጥሩ የመደለብ ብቃት አይኖራቸውም። ደካማ፣ ቀጭን፣ በመጠን አናሳ፣ ዝቅተኛ ክብደት ያላቸው፣ የታመሙ እና አካላዊ ቅርጻቸው የተበላሹ በጎች ለማደለብ መመረጥ የለባቸውም።

የአካል ሁኔታ ምዘና:

የበጎች የአካል ሁኔታ በውጫዊ ዕይታ እና ዳሰሳ መገምገም ማለት ነው። በአካል ሁኔታ በመመርኮዝ ከ1-5 ነጥቦች መሠረት ደረጃ ይሰጣቸዋል። በአብዘኛው ጊዜ አማካይ በግ ከ 2-3.5 ነጥብ ይሰጣቸዋል።



ክፍል 2፡ የሚደልቡ በጎችን መምረጥ

ለአካል ሁኔታ ምዘና ለማከናወን የጎድን አጥንት፣ ሽንጥ፣እና ፍሪምባ አከባቢ በመዳሰስ መወሰን ይቻላል። አማካይ የአካል አቋም ላይ የሚገኙ በጎች (ቀጭንም ወፍራምም ያልሆኑ) ተመራጭ ናቸው ምክንያቱም ለሚመገቡት መኖ ምላሻቸው ፈጣን ነው እና በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ውጤት የሚያመጡ እና በበቂ ሁኔታ ከተመገቡ ጠቦቶች ይልቅ ጥሩ ውጤት ያላቸው ናቸው የበጉን ሁኔታ መመርመር በቀላሉ በእይታ ብቻ ወይም በአከርካሪው አካባቢ፣ የጎድን አጥንት እና ዳሌው አካባቢ በመነካካት መለየት ይቻላል። በእጅጉ የከሱ እና ቀጭን እንስሳቶች ለማገገም ረዥም ጊዜ ይፈጃሉ። ከ15 ኪግ በታች የሚመዝን በግ ለማደለብ መግዛት አይመከርም።

ዝርያ:

የዝርያ አይነቶችን ለማደለብ አላማ መምረጥ በዋነኛነት በተለየ ቦታ ባሉ የዝርያ አይነቶች ላይ ይመረኮዛል። ይህ ተግባራዊ የሚደረገው በገጠራማው አነስተኛ፣ ከተሞች፣ የከተማ ዳርቻዎች እና የህብረት ስራ የበግ ማደለብ ስራ አከናዋኞች ላይ ተግባራዊ የሚሆን ነው በርካቶች ከሌላ ክልሎች ስለሚመጡ ዝርያዎች እውቀት የላቸውም። በኢትዮጵያ ውስጥ በመላው አገሪቱ በአፈጻጸም፣ በጥራት ወይም በመደለብ አቅም ከፍተኛ ዋጋ በመኖሩ ምክንያት ተመራጭ ዝርያዎች ሜንዝ፣ ዶዮገና፣ ቦንጋ፣ ሆሮ እና ሌሎች የተሻሻሉ ብሆኑ ይመከራሉ።

ጾታ:

ወንዶች በዋነኝነት ለማደለብ ሁኔታ ይውላሉ እና ለሃይማኖታዊ አላማም ይመረጣሉ። ሴቶች በአብዛኛው ለርቢ አላማ ይተዋሉ።



ክፍል 3፡ የሚደልቡ በጎች አያያዝ

የክፍሉ ዓላማ

የዚህ ክፍል ዓላማው የተወሰኑ በበግ ማደለብ ስራ ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ የማርባት ተግባራቶችን መዳሰስ ነው። ይህ ምዕራፍ ለሰልጣኞች ስኬታማ የማደለብ ስራ ለይ የተሰማሩ አካላት ሊከተሏቸው የሚገቡ የማርባት ተግባራቶችን በተመለከተ ግንዛቤ ያስጨብጣል። እነዚህም ጥነኛ ተህዋሲያንን ማስወገድ፣ ክትባት መስጠት፣ ማኮላሸት፣ መጠለያ መስራት፣ የበሽታ ቁጥጥር እና አጠቃላይ አያያዝ ሲሆን ለበግ ማደለብ የራሳቸውን ሚና ይጫወታሉ።

ይህን የመማማር ክፍለ ጊዜ ሲያበቃ ሰልጣኞች የሚከተሉትን ማወቅ የሚገባቸው

- ✓ በበግ ማደለብ ስራ ላይ ጥቅም ላይ የሚውሉ የርቢ ተግባራቶችን መለየት
- ✓ የጤና ቁጥጥር፣ የትላትል ማስወገድና ክትባት አስፈላጊነት እና ዘዴዎችን መረዳት.
- ✓ የማኮላሸት ሁኔታን አስፈላጊነቱን መረዳት

ቅድመ እና ድህረ የግምገማ ጥያቄዎች:

1. በበግ ማደለብ ሂደት ላይ ዓበይት ተግባራቶች ምንድን ናቸው?

2. በጎችን ለማደለብ አዲስ የተገዙ በጎችን ለይቶ ማቆየት ያስፈለገው ለምንድን ነው?

3. የሚደልቡ በጎችን ከትላትል ነጻ ማድረግና ማስከተብ ያስፈለገው ለምንድን ነው?

4. የማኮላሸት ጥቅሙ ምንድን ነው?

5. የበሽታ ቁጥጥር፣ መከላከልና መቆጣጠር ዘዴዎች ምንድን ናቸው?

6. በበግ ማደለብ የተለመዱ በሽታዎች ምንድን ናቸው?

በግ የማደለብ ተግባር

የሚደልቡ በጎች ከተመረጡ እና ግዢው ከተከናወነ በኋላ ቀጥሎ የተመለከቱትን የእርባታ ተግባራት መገንዘቡ አስፈላጊ ነው።

ለይቶ ማቆየት፡

አዲስ የተገዙ ጠቦቶች ለተወሰኑ ቀናት በግዢ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ በሽታዎችን ለመለየት እንዲያስችል ተነጥለው መቀመጥ ይኖርባቸዋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ የሚታዩ ምልክቶች በተቻለ ፍጥነት ለማከም አስፈላጊ ናቸው።

ክፍል 3፡ የሚደልቡ በጎች አያያዝ

ከጥገኛ ተህዋሲየሰን መድኃኒት እና ክትባት

ከጥገኛ ተህዋሲየሰን መከላከያ ህክምና፡ በጎችን በማደለብ ክብ ትል ፣ የኮሶ ትል እና የሳንባ ትል ጥቃት ከፍተኛ የገንዘብ ኪሳራ ያስከትላል ስለሆነም ከጥገኛ ተህዋሲየሰን ነጻ የማድረግ ሂደት ሁልጊዜ የማደለብ ስራው ሲጀመር መከናወን ይኖርበታል። ጥገኛ ተህዋሲየሰን ለማከም በተለምዶ ጥቅም ላይ የሚውሉ መድሃኒቶች የሚከተሉት ናቸው።

አልቤንዳዞል፡

መጠነ ሰፊ ጥቅም ያለው ጥገኛ ማጥፊያ ሲሆን ኮሶ፣ የሆድ ትል ለማስወገድ ይረዳል (የኦስቴርታጊያ እጭ አራተኛ እርከንን ጨምሮ)፣ የአንጀት ትሎችንና የሳንባ ትሎችን ለማስወገድ ይረዳል።

ኤርሜክቲን፡

ጥቅም ላይ የሚውለው በአንጀትና በጨጓራ ክብ ትሎች የሚመጡ ቁስለቶችን ለማከም እንዲሁም የሳንባ ትሎችን እና የውጭ ተዋህስያን የሆኑ እንደ ቅማል፣መዥገር፣ ቅማንዥር፣ እከክ እና ዝንብ የመሳሰሉት የሚፈጥሩትን ቁስለት ለማከም የሚረዳ ነው።

ፋሲኔክስ (ትሪካልቤንዳዞል)፡

መጠነኛ የአገልግሎት ጥቅም ያለው ቤንዚሚዳዞል ሲሆን ከፍተኛ ውጤት አለው። ባደጉ በጎች በመደበኛ የጉበት ክፍል (በረር ወይም ፋሺዎላ ሄፓቲካ) በዕጭ ደረጃ ላይ በሚገኙት ማለትም (ከ1-6 ሳምንት እድሜ ባላቸው) እና በእጭ (ከ6-9 ሳምንት እድሜ ባላቸው) ከፍተኛ ውጤት ያመጣል። በሁሉም በጉበት ውስጥ ባሉ እጮች ላይ ውጤታማ ነው። በእነዚህ እጮች ላይ ያለው ውጤት አስፈላጊ ነው ምክንያቱም እነዚህ እጮች ወደ ሃሞት የሚፈሱ በመሆኑ የጉበት ህብረ ህዋሳት ላይ ከፍተኛ ውድመት የሚያስከትሉ በመሆናቸው ነው። ጸረ-ጥገኛ መድኃኒቶችን መላመድ በበጎች ኢንዱስትሪ ውስጥ እያደገ የመጣው ችግር ነው ስለዚህ ጸረ-ትላትል መድኃኒቶች ውጤታማነታቸው እየቀነሰ መምጣቱ የተዋህስያን መላመድ እየጨመረ በመምጣቱ ምክንያት የኢኮኖሚ ኪሳራ ያስከትላል የሚል ስጋት አለ። ስለሆነም የአንቴልሚንቲክስ ተገቢ አጠቃቀም የመከላከል አቅም መጨመርን በተመለከተ መከላከል ስራ መስራት ያስፈልጋል።



ክፍል 3፡ የሚደልቡ በጎች አያያዝ

ክትባት

ክትባት በሽታዎችን ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ውጤታማ መንገዶች አንዱ ነው፡፤ የክትባት መርሃ ግብሮች በአካባቢው ባለው የበሽታ ስጋት፣ በወቅት ወይም የማደለብ ስራው በጎች ላይ በሚከናወንበት የዓመቱ ወቅቶች ላይ በመመርኮዝ በአካባቢው የእንስሳት ሐኪም ምክር የሚወሰን ይሆናል። በጎች ሁልጊዜም ለጎሮርሳ፣ ሳምባ ምች እና አባሰንጋ ይከተላሉ። መልቲ ቫይታሚን ክትባቶች መጠነ ሰፊ ግብአት እና ቫይታሚን ያካተቱ በመሆናቸው አስፈላጊ ናቸው። ቫይታሚን ኤ፣ ቫይታሚን ዲ፣ ቫይታሚን ኢ፣ ቫይታሚን ቢ1፣ ቫይታሚን ቢ2 ቫይታሚን ቢ 6፣ ኒኮቲናማይድ፣ ፓንቶቴኖል እና ቫታሚን ቢ 12 ያካተቱ ናቸው።



የበሽታ ቁጥጥር የሚከተሉትን ተግባራት ያካትታል፡

የበጎች ቁጥጥርና መረጃ አያያዝ፡

የበግ ማድለቢት ስራውን የሚያከናውን ግለሰብ እንደመሆኑ በመደበኛ ሁኔታ የስራውን ጤናማነት እና ምርታማነት ከፍ ለማድረግ እንዲችሉ የበሽታ ወይም የችግር ማናቸውንም ምልክቶች በጎችዎ ላይ መኖር አለመኖራቸውን እንዲመረምሩ ይመከራሉ። በጎችዎን ሲመረምሩ በጎቹ መደበኛ ባህርይ (ንቃት፣ የመንቀሳቀስ ነጻነትና፣ በንቃት መመገብ እና ማመንዠግ) እንዲሁም ያልተለመዱ የበግ ባህርያቶች እና የህመም ምልክቶች (በቆሰለ እግር የተነሳ ማነከስ፣ ቁስል፣ እብጠት ወይም ጉዳቶች፣ ያልተለመደ ገጽታ ወይም ባህርይ፣ ማስቀመጥ፣ የማያቋርጥ ሳል፣ ከፍተኛ የክብደት መቀነስ እና የመኖ ፍላጎ ማጣት) ሁኔታዎች መዳሰስ ይኖርባቸዋል፡፤ ከምርመራው በተጨማሪ የበሽታ አይነቶች፣ የህክምና ቀንና አይነት፣ የመድሃኒት አይነትና መጠን የመሳሰሉ የጠቅላላ ጤና መረጃዎች መመዝገብ ያስፈልጋል።

መከላከልና ቁጥጥር:

የበግ አደላቢዎች የኢትዮጵያን የህክምና የጊዜ አቆጣጠር መከተል አለባቸው። አነስተኛ መጠን ያላቸው እንስሳቶች የህክምና ጊዜ ቀመር የእሴት ሰንሰለት የመንዝ፣ ቦንጋና ዶዮ ገና ሳይቶች ዝቅ ብሎ ሰንጠረዥ 1 ላይ ተመልክተዋል።

ማኮላሸት፡

ይህ ከሙክቶች ላይ በፍጥነት ማደግ እንዲችሉ እና እንዲወፍሩ የወንዴ ዘር እንዳያመርቱ የወንዴን ዘር ማስወገድ ነው።

የስልጠና ማኑዋል

ክፍል 3፡ የሚደልቡ በጎች አያያዝ

ሰንጠረዥ 1፡ አነስተኛ እንስሳቶችን የዋጋ እሴት ሰንሰለት ሳይቶች በተመለከተ የኢትዮጵያ የህክምና ቀን መቁጠሪያ

የመንጋ የጤና ምርመራ	መንዝ	ዶሮገና	ቦንጋ
አነስተኛ እንስሳቶችን አንጀት ተዋህስያን እና ለሳንባ ጥገኛ መከላከል እና ማከም	ጥቅምት፣ታህሳስ የካቲት፣ ሰኔ	ጥቅምት፣ጥር፣ የካቲት፣ ሰኔ	ጥቅምት፣ መጋቢት፣ ሰኔ
የጨጓራ እና የአንጀት ተዋህስያንን ለመቆጣጠር አርሶ አደሮችን ማሰልጠን	መስከረም፣ ጥቅምት፣ ታኅሣሥ	ታኅሣሥ፣ጥር፣ ሚያዝያ	ታኅሣሥ፣ ግንቦት
አቫይን ፓስቱሮሎሲስ መከተበብ	ጥቅምት፣ መጋቢት/ሚያዝያ	የካቲት፣ ነሐሴ	ኅዳር፣ሚያዝያ
የአነስተኛ አመንዥኮኪ ደስታ መሰል በሽታ ክትባት	መስከረም፣ ጥቅምት፣ ኅዳር	ታኅሣሥ	ታኅሣሥ
የበግ ፈንጣጣ ክትባት	መስከረም፣ ጥቅምት	ሚያዝያ	ሚያዝያ
አርሶ አደሮችን በበጎች የመተንፈሻ አካል ህመም ቁጥጥር ላይ ማሰልጠን	መጋቢት	ታኅሣሥ፣ ግንቦት	መጋቢት

የስልጠና ማኑዋል

ክፍል 3፡ የሚደልቡ በጎች አያያዝ

በማደለብ ሂደት በጎች ለስርያ አላማ የማይውሉ በመሆናቸው ፈጣን ክብደት መጨመር እና የስብ ማከማቸት ብቃት አላቸው። በጎች ሲኮላሹ በእንስሳት ሐኪሞች ድጋፍ በሚሰጡ እንደ ቡርዲዞ የመሳሰሉ ቁሳቁሶች መጠቀም አለባቸው። አንዳንድ አርሶ አደሮች በድንጋይ የወንዴ ዘሮችን የመቀጥቀጥ እና የመሳሰሉ ባህላዊ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ይህውም በወንዴ ዘር ላይ ከባድ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል እና በጎቹን ለእልፈት ሊዳርገው የሚችል ነው።



የመጠለያ ሁኔታ

በጎች ለማዳ እንስሳ እንደመሆናቸው ሁልጊዜም በቡድን መጓጓዝና መቆየት ወይም ቢያንስ ሁልጊዜ የተለያዩ በጎችን ማየት እንዲችል በጥንድ በጥንድ መሆን ይኖርባቸዋል።

በአጠቃላይ የመጠለያ ዋና ዓላማ ከአየር ንብረት ጫናዎች (ከፍተኛ ሙቀት፣ ቅዝቃዜ፣ ዝናብ፣ ነፋስ ወዘተ) ለመከላከል ሲሆን ለበጎች አካላዊ ሁኔታ ተስማሚ አካባቢን ለመፍጠር ፣ ከአዳኝ አውሬዎችና ከስርቆት ለመከላከል ነው። ተጨማሪ ወጪዎችን ለማስወገድ መጠለያ በአከባቢው ባሉ ቁሳቁሶች (እንጨት፣ ጡብ) ከምስራቅ ወደ ምዕራብ አቅጣጫ መገንባት ይኖርበታል። በተጨማሪም ንጹህ፣ ጥሩ የአየር ዝውውር ያለው፣ በቆላማ አከባቢዎች ሙቀት እና በደጋማ አከባቢዎች ዝናብ እና ብርድ የሚከላከል መሆን አለበት። ፈሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦይ ልነረው ይገባል።

በማደለብ ስራ ውስጥ በጎች የሚመገቡትን ወደ ምርት ቶሎ በመቀየር ለገበያ በቂ የሆነ ክብደት ሊኖራቸው ይገባል። በመሆኑም እንቅስቃሴዎችን በማደለብ ወቅት የሚገታ እና ውሱን እንቅስቃሴ ብቻ እንዲኖራቸው ማድረግ ያስፈልጋል። የቦታ ፍላጎት በእያንዳንዱ እንስሳ በተቀራራቢ ቦታ 2 ካ.ሜ ነው።

ተጨማሪ ንባብ፡

መኮንን፣ ኤም፣ አሰፋ፣ ኤ፣ ናኔ፣ ቲ፣ አየለ፣ ኤፍ፣ አርኬ፣ ኤ፣ ኤሊያስ፣ ቢ እና ዌላንድ፣ ቢ.2009። አነስተኛ እንስሳት ጤና ምርምራ ካላንደር በኢትዮጵያ፣ ናይሮቢ ኬኒያ፡ ኢሊሪ
https://hdl.handle.net/10568/107144

የስልጠና ማኑዋል

ክፍል 4፡ መኖ እና የሚደልቡ በጎች አመጋገብ

የክፍሉ ዓላማ

መኖ በግ ማድለብ ላይ መሠረታዊ ጉዳይ ነው። የመኖ አቅርቦት (ብዛት)፣ የምግብነት ይዘት(ጥራት) እና ዋጋ ሁሉም የበግ እንክብካቤ እና የእርባታ መስፈርቶችን ለማሟላት መታሰብ አለበት። በግ አድላቢ እንደመሆንዎ የሚያደለቡትን በግ ምን፣ እንዴት እና መቼ እንደሚመገቡ ማወቅ አለቦት። ይህ ክፍለ ጊዜ የበግ ማድለብን በተመለከተ ጠቃሚ መረጃ ለመስጠት ያለመ ነው።

በዚህ የትምህርት ክፍለ ጊዜ መጨረሻ ላይ ሰልጣኞች የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፡-

- "የአመጋገብን ትርጉም ይረዳሉ
- የበጎችን የአመጋገብ ፍላጎቶች በደንብ ያውቃሉ።
- ለበግ ማድለብ የመኖ ግብዓቶችን ይለያሉ።
- ስለ ተሻሻሉ የመኖ አመራረት ስርዓቶች ያውቃሉ።

የቅድመ እና ድህረ ግምገማ ጥያቄዎች፡-

1. አመጋገብ ምንድነው ነው?
2. በግ ለማድለብ የሚያስፈልጉት የአመጋገብ መስፈርቶች ምንድናቸው?
3. ለበግ ማድለብ ያሉ መኖዎች ምንድናቸው?
4. ለበግ ማድለብ በጣም ጥሩው የመመገቢያ ዘዴ ምንድነው?
5. የተሻሻሉ የመኖ አመራረት ሥርዓቶች ዓይነቶች ምንድናቸው?

ክፍል 4.1. በግ ለማደለብ የምግብነት ፍላጎት

የተመጣጠነ መኖ በጎችን በማድለብ አጠቃላይ ምርታማነት፣ ጤና እና ደህንነት ላይ ትልቅ ሚና ይጫወታል። የበግ አድለቢያዎች ለሥነ-መኖ አያያዝ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው። በበጎች የሚፈለጉ አምስት ዋና ዋና የመኖ ዓይነቶች ናቸው። እነዚህም ውሃ፣ ኃይል ሰጪ፣ ፕሮቲን፣ ቫይታሚኖች እና ማዕድናት ናቸው።

ውኃ፡

ውሃ የእንስሳት አካል ዋና ክፍል በመሆኑ በበርካታ ምክንያቶች ተጽዕኖ ይደረግበታል እነዚህም እንደ ዝርያ፣ ዕድሜ እና አመጋገብ በሰውነት ውስጥ ያለውን መጠን ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ሁኔታዎች ናቸው። እንስሳት ከመኖ ይልቅ ለውሃ እጥረት የበለጠ ተጠቂ ናቸው ምክንያቱም ውሃ ለመኖ መፍጫ፣ ማዋሃጃ፣ ለደም ዝውውር እጂግ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ የውሃ ፍጆታቸው የተገደበ ከሆነ የመጀመሪያው ምልክት የመኖ ፍጆታ ይቀንሳል። የውሃ ፍጆታ አነስተኛ ከሆነ ፈጣን ክብደት የመቀነስ እና ሰውነት ድርቀት ይከሰታል። የውሃ መጠን 10 በመቶ በሰውነት ውስጥ መቀነስ አደገኛ እንደሆነ ይቆጠራል። የውሃ ጥራት እጅግ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ የመኖ አወሳሰድን እና የእንስሳት ጤናን ሊጎዳ ይችላል። ዝቅተኛ ጥራት ያለው ውሃ ብዙውን ጊዜ ዝቅተኛ የውሃ እና የመኖ ፍጆታን ያስከትላል። መሠረታዊ የውሃ ምንጮች የመጠጥ ውሃ፣ በመኖ ውስጥ ያለ ውሃ እና የምግብ መፈጨት ሂደት ውስጥ ያለ ውሃ ናቸው።

የስልጠና ማኑዋል

ክፍል 4፡ መኖ እና የሚደልቡ በጎች አመጋገብ

ኃይል ሰጪ:

የኃይል እጥረት (ጠቅላላ ሊፈጩ የሚችሉ ንጥረ ነገሮች፣ TDN) በእንስሳት ማድለብ ውስጥ በጣም የተለመደ ነው። ካርቦሃይድሬት እና ስብ ዋናዎቹ የኃይል ምንጮች ናቸው ይህም በጎች የማድለብ TDN ከፍላጎታቸው በታች ከሆነ ያለውን ኃይል ለእድገትና ለበግ ምርት ወጪ ማስቀጠል ይጠቀማሉ። ስለዚህ በማድለብ ከፍተኛ ምርት ለማግኘት በቂ ሃይል ማቅረብ አስፈላጊ ነው። የተለመዱ እና ኢኮኖሚያዊ የኃይል ምንጮች የስንዴ ገለባ፣ የበቆሎ ገለባ፣ የአጃ እህል እና የእንሰት ቅጠሎች ናቸው።

ፕሮቲን:


እንስሳ ጉልበት ሲያጡ፣ በአመጋገብ ውስጥ የፕሮቲን እጥረት ሁኔታውን ያባብሰዋል። በጎች ለመደበኛ እድገታቸው እና ውፍረት ከፍተኛ መጠን ያለው ፕሮቲን ያስፈልጋቸዋል። የፕሮቲን ከ7% መሠረታዊ ፍላጎት በተጨማሪ ለተሻለ የስጋ ምርት በምግቡ ውስጥ ተጨማሪ መጠን ያስፈልጋቸዋል። ይህ ምክንያቱም ጠቦቶች በራሳቸው ውስጥ ብዙ የሚያስፈልጋቸውን አሚኖ አሲዶች የሚያቀርቡ ረቂቅ ተሕዋስያን ስላሏቸው ነው። የፕሮቲን ፍላጎት ሊፈጩ በሚችል ፕሮቲን (DP) ላይ ተመስርቶ ይሰላል።

ሠንጠረዥ 2U በኢትዮጵያ አነስተኛ የከብት እርባታ እሴት ሰንሰለት ውስጥ በተመረጡ ቦታዎች ላይ የተለያዩ የመኖ ሀብቶች ለመኖ ፕሮቲን ያላቸውን አስተዋፅኦ ያሳያል።


ዩሪያ በሰው ሠራሽ ፕሮቲን በጣም የበለፀገ በመሆኑ የእንስሳት ምግብነት በተወሰነ መጠን ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። በዕለታዊ ራሽን ከ1.5% (15 ግ) መብለጥ የለበትም። በእጅ መቀላቀል ትክክለኛ የሞላሰስ/የዩሪያ ድብልቅ ስለማይሰራ ዩሪያን ከሞላሰስ ጋር በፍጹም አትቀላቅሉ። በእጅ መቀላቀል በበጎች ውስጥ የዩሪያ መመረዝ የተለመደ ምክንያት ነው።

ክፍል 4፡ መኖ እና የሚደልቡ በጎች አመጋገብ

ምስል 2. በዶዮጋና (ሀ) እና በመንዝ (ለ) ውስጥ ለመኖነት የሚውሉ የኃይል ሰጪ ይዘቶች የመኖ ሀብቶች አስተዋጽኦ።



ምስል 3. በዶዮጋና (ሀ) እና በመንዝ (ለ) ውስጥ ላሉ ምግቦች አጠቃላይ የድፍድፍ ፕሮቲን ይዘት የመኖ ሀብቶች አስተዋፅኦ



የስልጠና ማኑዋል

ክፍል 4፡ መኖ እና የሚደልቡ በጎች አመጋገብ

ሊፈጩ በሚችሉ ፕሮቲን እና በአጠቃላይ ሊፈጩ የሚችሉ ንጥረ ነገሮች መካከል ያለው መጠን፡-

በጎችን ለማድለብ የቲዲኤን (TDN) ዕለታዊ ፍላጎት ከሰውነታቸው ክብደት በአማካይ 3-4% ነው። ለ DP እና TDN ዕለታዊ ፍላጎቶች መካከል ያለው መጠን 1፡4-4.5 ነው። የጠበበ የTDN መጠን የስጋ/የበግ ምርትን አይጨምርም። ነገር ግን በምትኩ የፕሮቲን አቅርቦት ትርፍ ወደ ካርቦሃይድሬት በመቀየር ወይም ወደ ዩሪያ በመውጣቱ ይባክናል። ፋይበር በአመጋገብ ውስጥም ግምት ውስጥ መግባት አለበት። ከፍተኛ መጠን ያለው ገለባ ወይም ድርቆሽ ወደ ፈጣን እርካታ ያመራል።

ማዕድናት:

ካልሲየም እና ፎስፈረስ በበጎች ድልብ በጣም ጠቃሚ ማዕድናት ናቸው። እነዚህ ለብዙ የእንስሳት ሜታቦሊዝም የሚመያሳልጡ ናቸው። እነዚህ በአጥንቶች እና ጥርሶች ውስጥ ባሉበት ቦታ ይከማቻሉ፤ አስፈላጊ ከሆነ ማውጣት ይቻላል። ቢያንስ 5-8% ፖታሺያም እና 10% ካልሺየም እንደ ማዕድን ተጨማሪዎች መደጎም ይቻላል። በማድለብ ሂደት የሚፈለገው መጠን ካሺየም: ፖታሺየም 1.5፡2.1 ነው። ትክክል ያልሆኑ ሬሾዎች የፊኛ ድንጋዮች እንዲፈጠሩ ሊያደርግ ይችላል።

የካልሺየም እና ፖታሺየም እጥረት ወደ መገጣጠሚያ እንቅስቃሴ ችግር፣ አጥንቶች እና ጥርሶች መዳከም፣ የኃይል አጠቃቀም መጓደል፣ የመኖ አወሳሰድ መቀነስ፣ ዝቅተኛ ክብደት መጨመር፣ እንጨት፣ ብረት እና ሱፍ ማኘክ ችግሮችን ያስከትላል።

ሶዲየም እና ክሎሪን ከፊል ማድለብ ሥርዓት ውስጥ በተለይም ደካማ የተፈጥሮ ግጦሽ ላይ አስፈላጊ ናቸው። ሶዲየም እና ክሎሪን በአብዛኛዎቹ የመኖ ራሽን ውስጥ ከሚገኙት በላይ በብዛት ያስፈልጋሉ፣ ስለዚህ ጨው በልቅ እንዲሰጥ የሚመከር ነው። የሲዲየም እና ክሎሪን እጥረት ምልክቶች የማያቋርጥ መንቀጥቀጥ እና የሚወዛወዝ የእግር ጉዞ፣ የመኖ ፍላጎት አለመኖር፣ የሰውነት ክብደት መቀነስ፣ ሻካራ በጠጥ እና ብረት እንጨት ማኘክ።

ቫይታሚኖች-

ሦስት ዋና ዋና ቫይታሚኖች ኤ፣ ኤስ እና ኢ በበቂ መጠን ያስፈልጋል። እነዚህ ብዙውን ጊዜ በአረንጓዴ መኖ ሣሮች ይገኛሉ። አረንጓዴ መኖ የማይገኝ ከሆነ ቫይታሚኖች ኤ፣ ዲ እና ኢ በምጥን ራሽን ውስጥ መቀላቀል አለበት። የቫይታሚን ኤ፣ ዲ፣ ኢ እጥረት ምልክቶች ማሳል፣ የአፍንጫ ፍሳሽ፣ የውሃ ዓይኖች፣ የቆዳ ቆዳ፣ የሳምባ ምች፣ ተቅማጥ እና አስገራሚ የእግር ጉዞን ያካትታሉ።

ሠንጠረዥ 2ሀ እና 2ለ በሞቃታማ አካባቢዎች ጠቦት የንጥረ-መኖ ፍላጎቶችን በተመለከተ መመሪያ ያሳያል።

ክፍል 4፡ መኖ እና የሚደልቡ በጎች አመጋገብ

ክፍል 4.2፡ መኖዎች

በግ ማድለብ ውስጥ ያለው አፈጻጸም፤ በአመጋገብ መስፈርቶች መሠረት አነስተኛውን ወጪ ራሽን በመመገብ ከፍተኛውን የዕለት ተዕለት ክብደት መጨመር ላይ የተመሠረተ ነው። ለፕሮቲን እና ለሃይል የሚያስፈልጉትን ፍላጎት ለማሟላት በመጠን እና በስብስብ በቂ ከመሆን በተጨማሪ የበግ መብል እንዲሁም እርስ በርስ የተያያዙ ባህሪያትን እና ፊዚዮሎጂያዊ ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት። አመስኮ እንስሳት ለውሃ እና ለመኖ ፍላጎቶች ያተኮሩ ሳይክሊካዊ እንቅስቃሴዎች እንዲሁም ለቆሻሻ እና ለመኖ መፈጨት ሂደቶች አስፈላጊ የሆኑ የእረፍት ጊዜያት አሏቸው። በጎች ከእጽዋት አኗኗራቸው ጋር አስደናቂ የሆነ የባህሪ መላመድን ያሳያሉ። በጎችን ለማድለብ ዋና ዋና መኖዎች ገለባዎች፣ የአግሮ-ኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶች፣ የአገር ውስጥ የቢራ ፋብሪካ ተረፈ ምርቶች፣ የቤት ውስጥ ምግቦች ተረፈ ምርቶች እና የእህል ምርቶች ማጣሪያ ናቸው።

አሰራማ መኖዎች፡

እነዚህ፤ በአንፃራዊነት ብዙ የማይፈጩ ቁሶችን የያዙ ግዙፍ መኖዎች ናቸው፣ ከ 18% በላይ ጥሬ ፋይበር ነው። እነዚህ በእርጥበት ይዘታቸው ላይ በመመስረት ሁለት ምድቦች ማለትም ደረቅ እና እርጥብ ሊሆኑ ይችላሉ።

በጎች ለማድለብ የተለመዱ የመኖ ምንጮች የተፈጥሮ ግጦሽ፣ የሰብል ቅሪቶች፣ አረንጓዴ የግጦሽ መኖዎች እና ድርቆሽ ናቸው። የእነዚህ አጠቃቀም እንደየአካባቢው ፣ በአካባቢው የሚበቅሉ ሰብሎች እና ተገኝነት ይለያያል። የሰብል ተረፈምርቶች ከደረቅ መኖ መጠን ከ 3-13% ባለው ክልል ውስጥ ዝቅተኛ ድፍድፍ ፕሮቲን አላቸው። የሰብል ተረፈምርቶች ኡደት ውስጥ የችግሮች ምንጭ እንደመሆናቸው መጠን አስፈላጊ እየሆኑ መጥተዋል። ዋና ዋና የግጦሽ ሰብሎች ከእህል በተጨማሪ ከፍተኛ መጠን ያለው የሰብል ተረፈምርቶች (ለምሳሌ የጤፍ ገለባ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ በቆሎ፣ ማሽላ)፣ የእህል ጥራጥሬ (ለምሳሌ ባቄላ፣ የሜዳ አተር፣ ሽምብራ፣ ምስር፣ ለውዝ ወዘተ)።

ምጥን መኖዎች፡-

ከፍተኛ መጠን ያለው ፕሮቲን፣ካርቦሃይድሬትስ እና ስብ ያለው የመኖ ወይም የመኖ ድብልቅ ከ 18% ያነሰ ድፍድፍ ፋይበር እና ብዙውን ጊዜ እርጥበት ዝቅተኛ ነው። ፤አልሚ መኖዎች በሃይል ወይም በፕሮቲን የበለፀጉ ውድ ናቸው። የአግሮ-ኢንዱስትሪ ተረፈ ምርቶች የግብርና ምርቶችን በማቀነባበር የተገኙ ውጤቶች፤ እንደ የስንዴ ገለባ፣ የቅባት እህሎች (የጥጥ ዘር ኬክ፣ ኑግ ኬክ)፣ ሸንኮራ አገዳ እና ሲትረስ። ከሰብል ቅሪቶች ጋር ሲነጻጸር፣ እነዚህ ምርቶች፤ ጠቃሚ በሆኑ ንጥረ ነገሮች እና በመዋሃድ ስብስባቸው ውስጥ በጣም ጥሩ ናቸው. የእንደዚህ አይነት ምርቶች የአመጋገብ ዋጋ በእጅጉ ይለያያል. ከ10-45 ኪሎ ግራም የሚመዝን ጠቦት ለማድለብ ተስማሚ የሆነ የተለመደ የማጎሪያ ድብልቅ፤ የሚከተሉትን መያዝ አለበት:

ደረቅ መኖ መጠን: 80-90%
ሊፈጭ የሚችል ፕሮቲን: 14-16%
ጠቅላላ ሊፈጩ የሚችሉ ንጥረ ነገሮች (TDN): 63-75%
ካልሲየም: 0.7-0.8%
ፎስፈረስ: 0.5-0.6%

የስልጠና ማኑዋል

ክፍል 4፡ መኖ እና የሚደልቡ በጎች አመጋገብ

የመኖ ሰብሎች:

ከመጠን በላይ ማስጋጥ በኢትዮጵያ የእንስሳት እርባታ ውስጥ ካሉት አሳሳቢ ችግሮች አንዱ ነው። የግጦሽ መሬቶች እንስሳት ስለሚሰማሩ የእጽዋት ጥንካሬ እየቀነሰ እና ብዙም ፍሬያማ ያልሆኑ እና ብዙም የማይጠቅሙ ዝርያዎች አከባቢውን መቆጣጠር ይጀምራሉ። የአፈር መሸርሸር እና የአፈር ለምነት መቀነስን ያስከትላል



በጓሮ የሚለሙ መኖዎች፡

የጓሮ መኖ ምርት በቤት ግቢ ውስጥ የሚለማ የመኖ ሰብል ነው። በእርሻ ቤት ጓሮዎች ውስጥ የግጦሽ ቦታዎች ወይም አጥር ውስጥ የመኖ ምርትን ለመጨመር ቀላል እና ፈጣን የአመራረት መንገድ ናቸው። የጓሮ የአፈር ለምነት ብዙውን ጊዜ ከፍ ያለ ነው፣ ስለዚህ የመኖ መሬቶች፤ በጣም ውጤታማ ሊሆን ይችላል። በ100 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ትንሽ ቦታ፤ በዓመት እስከ 150 ኪሎ ግራም ደረቅ ባዮማስ ማቅረብ ይችላል





Table 2a. Daily nutrient requirement of rams 5-30kg for maintenance and growth.

Body weight	Gain or loss	Dry matter intake		Diet density	Energy			Protein		Calcium	Phosphorus	Vitamin A	Vitamin D
(kg)	(kg)	(kg)	% live weight	(Mcal/ kg)	ME (Mcal)	TDN (kg)	FU (kg)	Total (g)	Digestible (g)	(g)	(g)	(1000 IU)	(IU)
5	50	0.10	2.0	4.3	0.44	0.12	0.15	36	29	1.8	1.3	0.50	35
	100	0.12	2.3	4.3	0.50	0.14	0.18	45	36	1.8	1.3	0.50	35
	150	0.13	2.7	4.3	0.57	0.15	0.20	48	38	1.9	1.3	0.50	35
	200	0.15	3.0	4.3	0.64	0.17	0.22	54	43	1.9	1.3	0.50	35
	250	0.16	3.2	4.3	0.69	0.19	0.24	58	46	2.0	1.4	0.50	35
	300	0.18	3.6	4.3	0.77	0.21	0.27	65	52	2.0	1.4	0.50	35
10	50	0.18	1.8	4.0	0.73	0.20	0.26	61	49	2.1	1.5	0.85	67
	100	0.21	2.1	4.0	0.84	0.23	0.30	70	56	2.1	1.5	0.85	67
	150	0.24	2.4	4.0	0.96	0.27	0.34	80	64	2.2	1.5	0.85	67
	200	0.27	2.7	4.0	1.07	0.30	0.38	90	72	2.3	1.6	0.85	67
	250	0.30	3.0	4.0	1.18	0.33	0.42	99	79	2.4	1.7	0.85	67
	300	0.32	3.2	4.0	1.20	0.36	0.46	108	86	2.5	1.7	0.85	67
15	50	0.26	1.7	3.8	0.99	0.27	0.35	82	66	2.6	1.8	1.28	98
	100	0.30	2.0	3.8	1.14	0.31	0.40	95	76	2.7	1.8	1.28	98
	150	0.34	2.3	3.8	1.30	0.36	0.46	109	87	2.7	1.9	1.28	98
	200	0.38	2.5	3.8	1.45	0.40	0.51	121	97	2.8	2.0	1.28	98

የከብትና ማጉያ

Body weight	Gain or loss	Dry matter intake		Diet density	Energy			Protein		Calcium	Phosphorus	Vitamin A	Vitamin D
(kg)	(kg)	(kg)	% live weight	(Mcal/ kg)	ME (Mcal)	TDN (kg)	FU (kg)	Total (g)	Digestible (g)	(g)	(g)	(1000 IU)	(IU)
	250	0.42	2.8	3.8	1.60	0.44	0.57	134	107	2.9	2.0	1.28	98
	300	0.46	3.1	3.8	1.75	0.48	0.62	146	117	3.0	2.1	1.28	98
20	100	0.41	2.0	3.5	1.42	0.39	0.50	119	95	3.1	2.2	1.70	133
	150	0.46	2.3	3.5	1.61	0.44	0.57	135	108	3.2	2.2	1.70	133
	200	0.51	2.6	3.5	1.80	0.50	0.64	150	120	3.4	2.4	1.70	133
	250	0.57	2.8	3.5	1.99	0.55	0.71	166	133	3.5	2.4	1.70	133
	300	0.62	3.1	3.5	2.18	0.60	0.77	182	146	3.6	2.5	1.70	133
25	100	0.47	1.9	3.1	1.47	0.41	0.52	122	98	4.0	2.8	2.12	168
	150	0.55	2.2	3.1	1.69	0.47	0.60	141	113	4.0	2.8	2.12	168
	200	0.62	2.5	3.1	1.91	0.53	0.68	160	128	4.1	2.8	2.12	168
	250	0.69	2.8	3.1	2.14	0.59	0.76	179	143	4.2	2.9	2.12	168
	300	0.76	3.0	3.1	2.36	0.65	0.84	198	158	4.3	3.0	2.12	168
30	100	0.64	2.1	3.0	1.92	0.53	0.68	161	129	4.6	3.2	2.55	200
	150	0.73	2.4	3.0	2.18	0.60	0.77	182	146	4.7	3.2	2.55	200
	200	0.81	2.7	3.0	2.44	0.67	0.87	204	163	4.8	3.3	2.55	200
	250	0.90	3.0	3.0	2.69	0.74	0.95	225	180	4.9	3.3	2.55	200
	300	0.98	3.3	3.0	2.95	0.81	1.05	248	198	5.0	3.3	2.55	200

Note: Mcal, megacalorie; ME, metabolizable energy; TDN, total digestible nutrients; FU, feed units; IU, International unit.
Source: Kearl, 1982.

Կենդանի ապրանք

Table 2b. Daily nutrient requirement of rams 30-90kg for maintenance and growth.

Body weight	Gain or loss	Dry matter intake		Diet density	Energy			Protein		Calcium	Phosphorus	Vitamin A	Vitamin D
(kg)	(kg)	(kg)	% live weight	(Mcal/ kg)	ME (Mcal)	TDN (kg)	FU (kg)	Total (g)	Digestible (g)	(g)	(g)	(1000 IU)	(IU)
30	120	1.15	3.8	2.25	2.59	0.72	0.92	113	62	5.9	3.2	3.2	185
40	110	1.43	3.6	2.15	3.07	0.85	1.09	137	74	6.3	3.5	4.2	222
50	100	1.69	3.4	2.05	3.48	0.96	1.23	159	84	6.8	3.8	5.2	277
60	100	1.94	3.2	2.05	3.99	1.1	1.41	181	96	7.2	4	6.3	333
70	80	2.18	3.1	1.9	4.08	1.13	1.45	194	98	7.5	4.3	7.3	388
80	80	2.41	3	1.9	4.51	1.25	1.6	212	108	7.9	4.4	8.3	444
90	80	2.63	2.9	1.9	4.92	1.36	1.74	231	118	8.3	4.7	9.3	499

Note: Mcal, megacalorie; ME, metabolizable energy; TDN, total digestible nutrients; FU, feed units; IU, International unit.
Source: Kearl, 1982.





ከምግብ ሰብሎች ጋር በስብጥር መዝራት እና መትከል:-

የመኖ ሰብሎችን ከምግብ ሰብሎች ጋር በፈረቃ፣ በስብጥር፣ ወይም በውስጣቸው ማልማት ይቻላል። በኢትዮጵያ የተለመደው አጃ-ቬች እና አጃ-ባቄላ ናቸው።

የግጦሽ መኖዎች:

የመኖ ሰብሎች በምግብ ሰብሎች መስመሮች መካከል ማልማት ዘዴ ነው። የአፈር መሸርሸርን ይከላከላሉ እና የአፈርን ለምነት ያሻሽላሉ፣ የዛፍ ጥራጥሬዎች ከሆኑ እንጨት ለነዳጅ እና ለመጠለያ ይሰጣሉ እና ለመሰል ጉዳዮች ጥቅም ላይ ይውላሉ።



ምሳሌዎች፤ ዴሾ (ፔኒሴተም ፔዲካላተም) እና የዛፍ ሉሰርን (ቻማዬሳይቲሱስ ፓልሜንሲስ) ያካትታሉ።

አገር በቀል መኖ ሰብሎች ልማት:-

በተፈጥሮ በአከባቢ የሚገኙ የመኖ ዕጽዋቶች እንስሳት መኖ እስከ ሩብ የሚደርስ ድርሻ ይይዛል። ይሁን እንጂ የእነዚህ ዕጽዋቶች በእንስሳት ምርት እና ምርታማነት ላይ በቂ መረጃ ይጎድላቸዋል። የነዚህን ዝርያዎች እድገት እና የእንስሳት ላይ ያላቸው አስተዋጾ መረጃዎችን በማመንጨት ምርምርና ልማትን ለማስፋፋት ባለድርሻ አካላት ሊጠቀሙበት ይገባል። ከእንደዚህ ዓይነት መኖዎች የመነጩ የመጀመሪያ ደረጃ ውጤቶች ማለትም ቦትሪኦክሊን ሺምፔሪ፣ ብሩግማንሲያ ሱዋቪኦለንስ በርች፣ ባሴላ አልባ እና ኤሪትሪና አቢሲኒካ፣ በበግ እርባታ እና በግን በማጥባት ለክብደት መጨመር፣ እና እርባታ ብቃታቸው ከምጥን መኖዎች አንጻር ለመተካት የተካሄዱ ጥናቶች ተስፋ ሰጭ ናቸው።

አብዛኛዎቹ እነዚህ አገር በቀል መኖዎች ፀረ-አልሚ ንጥረ ነገሮችን ይዘዋል፣ ይህም ከመመገባቸው በፊት ምርመራ እና ፍተሻ ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ የኢትዮጵያ አገር በቀል መኖዎች መለየት፣ መገምገም ያስፈልጋል። እና በዚህ ተለይቶ ይታወቃል።









ሙሉቀን ዘለቀ: ሞኝ አበባ፣ ብሩግማንሲያ ሱዋቬኦሌንስ በር'ችት አቀነባብሮ በመቀቀል ለበጎች መመመገብ።

የኬሚካል / የተመጣጠነ ንጥረ ነገር ስብስብ የተለመዱ ምግቦች እና ለተመረጡ ቦታዎች የሚመከሩ የንጥረ ነገሮች ጥምረት፤ በሰንጠረዥ 3 ይታያሉ።

ክፍል 4. 3፡ ዕለታዊ መኖ አመጣጠን

የዕለታዊ መኖ ቀመር ንጥረ ነገሮችን መምረጥ እና መመደብን የሚያካትት እንዲሁም በዝቅተኛ ዋጋ ለተፈለገው የምርት ደረጃ በቂ ንጥረ ነገሮች ማቅረብን መሰረት ያደረገ ነው። አንድ ራሽን የመኖ መጠን በ24 ሰዓት ጊዜ ውስጥ ለእንስሳት ይመገባል።







በግ ለኃይል፣ ፕሮቲን፣ ማዕድናት (በተለይ ካልሲየም እና ፎስፎረስ) እና ቫይታሚኖች በትክክል የተመጣጠነ መኖ መመገብ አለበት። በግ የተመጣጠነ መኖ የማይመገቡ ከሆነ የአመጋገብ ፍላጎቶቻቸውን ማሟላት ላይችሉ ይችላሉ። የራሽን ማመጣጠን አነስተኛውን ወጪ የመመገብ አማራጮችን ለመወሰን ይረዳል። ወጪ በማድለብ ኢኮኖሚ ውስጥ በጣም አስፈላጊ ነው።

ሬሽን ለማመጣጠን አምስት ደረጃዎች ናቸው።

- ✓ የሚመግቡትን በጎች እድሜ እና ክብደት አንፃር ይግለጹ፤
- ✓ የመኖ ፍላጎቶቻቸውን ይመልከቱ፣
- ✓ ምን ዓይነት መኖዎች ይገኛሉ የሚለውን ይወስኑ፤
- ✓ የምግቡን ንጥረ ነገር ስብጥር ይዘርዝሩ፣
- ✓ ሬሽኑን በእጅ ያመዛዝኑ ወይም የኮምፒውተር ሶፍትዌር ይጠቀሙ።

© ሙሉቀን ዘለቀ፡ ኮርች መሰብሰብ፣ ማድረቅ እና መመገብ፣ ኤሪትሪና አቢሲኒካ፣ በቦንጋ

ተጨማሪ ንባብ:

አሸራፍ አልኽቲብ፣ ጄን ዋማቱ (12/2/2020) ለበጎች አነስተኛ ዋጋ ያለው የራሽን ፎርሙላ መሣሪያ https://hdl.handle.net/20.500.11766/10787 ኪርል፣ ኤል. 1982. በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ውስጥ የከብት እርባታ ዕለታዊ የአመጋገብ ፍላጎቶች። ዩታ ስቴት ዩኒቨርሲቲ.

የአመጋገብ ስርዓት

በጎችን ለማድለብ ጥሩ የተመጣጠነ የአመጋገብ ስርዓት ስብስብ፤ በግምት 70% ምጥን እስከ 30% ሸካራቂዎች እንደሚከተለው መሆን አለበት ።

ሠንጠረዥ 3. በመንዝ፣ ቦንጋ እና ዶዮጌና ያሉ የተለመዱ የኢትዮጵያ ምግቦች።

አካባቢ	መኖ	DM (%)	ASh (%)	OM (%)	N (%)	CP (%)	NDF (%)	ADF (%)	ADL (%)	ME	IVDOM (%)
ቦንጋ	የተቆላ የተፈጨ ባቄላ	89.2	4.0	96.0	4.5	28.0	30.9	17.9	1.3	9.1	64.3
ቦንጋ	የተቆላ የተፈጨ ገብስ	90.4	3.5	96.5	1.7	10.4	37.6	10.3	2.3	10.6	72.5
ቦንጋ	የተፈጨ ስንዴ	84.9	2.4	97.6	1.9	11.8	17.6	4.0	0.9	3.8	28.7
ቦንጋ	የተፈጨ በቆሎ	82.6	2.0	98.0	1.5	9.5	18.7	4.9	0.8	11.9	78.5
ቦንጋ	ካቲካላ አተላ	95.5	13.6	86.4	3.9	24.1	46.2	22.3	5.3	5.3	60.2
ዶዮጋና	የስንዴ ገለባ	89.3	5.1	94.9	2.7	16.6	47.0	15.7	4.1	9.9	68.0
ዶዮጋና	የኑግ ኬክ	91.2	9.5	90.5	5.1	32.1	36.4	31.2	12.5	8.5	64.0
ዶዮጋና	የአካባቢ የማዕድን አፈር (ቦሌ)	82.1	14.9	85.2	0.2	1.0	4.4	13.2	2.2	3.2	24.0
መንዝ	የስንዴ ገለባ	88.9	4.9	95.1	2.5	15.6	46.3	15.3	3.2	8.7	60.6
መንዝ	የኑግ ኬክ	91.8	11.4	88.6	5.7	35.8	30.6	24.8	9.0	8.4	64.8
መንዝ	ምስር	90.2	5.4	94.6	4.3	27.0	30.4	24.8	4.5	6.8	52.2

ማስታወሻ: DM፣ ደረቅ ክፍል፣ OM ኦርጋኒክ ክፍል፤ N፣ ናይትሮጅን፤ CP፣ ጥሬ ፕሮቲን፤ NDF፣ መካከለኛ ፋይበር፤ ADF፣ አሲድ አጣቢ ፋይበር፤ ADL አሲድ ሊግኒን፤ ME፣ ኃይል፤ IVODM፣የልሜት መጠን

የአመጋገብ ስርዓት



አርሶ አደሮች በተፈጥሮ መኖዎች 30% የምርት ወጪን መቆጠብ ይችላሉ ተብሎ ይገመታል። ከፍተኛ ምግብነት ያለው መኖ ድብልቅ ከትንሽ ገለባ ጋር በተቀላቀለ ሼዶች ውስጥ መሰጠት ይመረጣል።

ክፍል 4.4: የመኖ ጥራት ደህንነት ቁጥጥር

የሚከተሉት የጥራት መለኪያዎች፤ ግምት ውስጥ መግባት አለበት:

ጥራት ያለው መኖ ለምርታማነት የሚያስፈልጉ ንጥረ-ነገሮች በተመጣጣኝ ደረጃ ይዞ መገኘት ስሆን ከማናቸውም የጤና ጠንቆች ነጻ መሆን አለበት። የእንስሳት መኖ እና ጥራት ከጥተኛ ተያያዥነት አለው።

የመኖ ጥራት እና ደህንነት ፍተሸ መስፍርቶች

የእይታ ገጽታ:

የመኖ ግብዐቶች ትክክለኛው ቀለም ሊኖረው እና ምንም ድብልቆች እንደ ጠጠር፣ ነፍሳት፣ አቧራ፣ ሻጋታ ወይም ፈንገስ እና ሌሎች የውጭ ነገሮች ልኖሩ አይገባም።

የጣት ሙከራ:

የመኖ ንጥረ ነገሮችን የሚፈለገው የእርጥበት መጠን፣ በጣም እርጥብ እና ደረቅ መሆን የለበትም። ከፍተኛ እርጥበት ወደ መፍላት እና ሻጋታ ያስከትላል።

ጊዜ ከፍ ያለ ነው፣ ስለዚህ የመኖ መሬቶች፤ በጣም ውጤታማ ሊሆን ይችላል። በ100 ካሬ ሜትር ስፋት ያለው ትንሽ ቦታ፤ በዓመት እስከ 150 ኪሎ ግራም ደረቅ ባዮማስ ማቅረብ ይችላል

የአመጋገብ ስርዓት



የመኖ ንጥረ ነገሮችን በማሸተት ማረጋገጥ በጣም አስፈላጊ ነው፣ ምክንያቱም አብዛኛዎቹ ንጥረ ነገሮች ጥራታቸው እንኳን ቢሆን አይቀንስም ሁልጊዜ የቀለም ለውጥ አያሳዩም።

ጣዕም እና ቃና:
ንጥረ ነገሮች ጥራት የሌላቸው ወይም የተበላሹ መሆናቸው በእንስሳት አለመቀበል በቀላሉ ሊታወቅ ይችላል።

የኬሚካል ቁጥጥር:
ይህ በልዩ ላብራቶሪ ውስጥ ብቻ ይከናወናል።

የመኖ ማከማቻ መጋዘን:
ሊበላሹ የሚችሉ ምግቦች፤ ለአጭር ጊዜ መቀመጥ አለበት።

ክፍለ ጊዜ 5. በጎችን ማድለብ እንደ ንግድ

ክፍል 5.1፡ የንግድ ሥራ ፈጣሪነት

የንግድ ሥራ ፈጠራ እና የአስተዳደር ችሎታዎች እጥረት አርሶ አደሮች በንግድ በግ እርባታ እንደ ተግዳሮት የሚታዩ ነገሮች ናቸው። በአለም አቀፉ የግብርና ምርምር በደረቅ አካባቢዎች (ICARDA) በኢትዮጵያ አነስተኛ የእንስሳት እርባታ ስራዎች፤ በግ ማድለብ ላይ ትኩረት የንግድ ቴክኒኮችን በመጠቀም የማድለብ ልማዳዊ ቴክኒኮችን ከማድለብ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ የተጣራ ትርፍ እንደሚያስገኝ አሳይቷል። ነገር ግን በአርሶ አደሮች ዘንድ ንግድን ላይ የተመሰረተ ማድለብ ላይ ዝቅተኛ ነው።

ይህ ክፍለ ጊዜ የበግ አርቢዎችን በግል ወይም በቡድን/በጎብረት ሥራ ማህበራት የማድለብ አቅምን ማሳደግ፣ ሥራቸውን ውጤታማ በሆነ መንገድ ማቀድ፣ ማደራጀት፣ መምራት፣ መተግበር፣ መከታተልና መገምገም ላይ ግንዛቤ ለማስጨበጥ ያለመ ነው።

የውይይት ነጥቦች

- ✓ የበግ ማድለብ ሥራ እንዳትሠራ እየከለከሉህ ያሉ ሁሉንም ነገሮች ይዘርዝሩ።
- ✓ ከላይ ለተዘረዘሩት ነገሮች ለእያንዳንዱ የተወሰነ መፍትሄዎችን ያዘጋጁ።
- ✓ የተሳካ ንግድ እንዲኖር የሚያስፈልጉ ባህሪያት ምንድናቸው።
- ✓ ስኬታማ ንግድ እንዲኖር ምን ዓይነት ችሎታዎች ያስፈልጋል።

የተዛባ አመለካከት ወይም መንገድ ክስተቶች በእውነታው ላይ ተጽዕኖ ያሳድራሉ ተብሎ ይታመናል እና ወደ አላስፈላጊ አቅጣጫዎች ያመራል። ስለዚህ የአመለካከት ለውጦች ማንኛውንም ክስተት ለመቆጣጠር እና ወደ ግለሰባዊ ፍላጎቶች ለመቅረጽ ይረዳሉ።

ስኬት ለሁሉም ሰው ይቻላል፤ ግን ለማግኘት ቀላል አይደለም። ግቦችን ማውጣት፣ ማቀድ፣ እድል መፈለግ፣ ጽናት፣ ቁርጠኝነት፣ በራስ መተማመን፣ የመረብ፣ አደጋዎችን ለመጋፈጥ ፈቃደኛነት፣ የማሳመን ችሎታ እና መረጃ መፈለግን ያካትታሉ።

ለስኬታማ የንግድ ሥራ ፈጣሪነት የመጀመሪያ ደረጃ፤ ትክክለኛውን የንግድ ሥራ ሀሳብ መፍጠር ነው። ስኬታማ ሥራ ፈጣሪ ሌሎች ሰዎች ማየት የማይችሉትን ችግሮች ማየት መቻል አለባቸው። ትልቁ የንግድ ሥራ ፈተና የንግድ ሀሳቡን ካሉት እድሎች ጋር ማዛመድ እና ወደ እውነታነት መለወጥ ነው። ለጀማሪዎች አዲስ ካፒታል ማግኘት ከመጀመሪያው ሀሳብ እና የንግድ ፕሮፖዛል ልማት በኋላ ዋናው ፈተና ነው። ከምርት ጀምሮ ምርቱን ወይም አገልግሎቱን ለደንበኛው ለማድረስ ሂደት ማርኬቲንግ በመባል ይታወቃል። ምርጡን ዋጋ ለማግኘት፣ የሰባ በግ እንዴት እና የት እንደሚሸጥ ማወቅ አስፈላጊ ነው።

ከዚህ በታች እንዳለው ለበግ ማድለብ ሥራ የንግድ ሥራ ሞዴል ለማዘጋጀት ይጠቅማል፣ ምክንያቱም የንግድ ሥራ ሐሳብዎን ለመግለፅ እና ለማሳወቅ ይጠቅማል።

ክፍለ ጊዜ 5. በጎችን ማድለብ እንደ ንግድ

ምስል 4. ለበግ ማድለብ የቢዝነስ ሞዴል

<table>
<tr><td>ችግር
ደካማ ገበያ ትስስር
ደካማ የመደራደር አቅም
አነስተኛ ግብዓት አቅርቦት
ውስን ችሎታ እና እውቀት</td><td>መፍትሄ
የጋራ ማድለብ እና ግብይት</td><td colspan="2">ልዩ እሴት
ጥራት ያለው ምርት በተመጣጣኝ ዋጋ ማቅረብ</td><td>ደንበኞች
ነጋዴዎች፣ ስጋ ቤቶች፣ ሆቴሎች እና ቀጥተኛ ሸማቾች</td></tr>
<tr><td>ነባር አማራጮች
ተሻሽሏል። የማድለብ ችሎታ እና ቴክኖሎጂ
ትብብር ማደለብ</td><td>ቁልፍ መለኪያዎች
ጥራት ያለው የሰባ በግ
የሰለጠኑ አባላት ቁጥር</td><td>የከፍተኛ ደረጃ ፅንሰ-ሀሳብ
የስራ እድል ፈጠራ እና ዘላቂ የገንዘብ ደህንነት</td><td>የንግድ መስመሮች
ቀጥታ ቻናሎች</td><td></td></tr>
<tr><td colspan="2">የወጪ መዋቅር
የመኖ ወጪ፣ የገንዘብ ቀረጻ እና ግብር</td><td colspan="3">የገቢ መስመር
ከበግ ሽያጭ፣ ከአባላት ግብይት ክፍያ፣ ከቁጠባ የሚገኝ ትርፍ</td></tr>
</table>

ተጨማሪ ንባብ:

ኢሳያስ ሙላቱ፣ ጄን ዋማቱ። (1/10/2020) የኢንተርፕረነርሺፕ እና የንግድ ችሎታዎች እድገት የስልጠና መመሪያ. ቤሩት፣ ሊባኖስ፡ በደረቅ አካባቢዎች የግብርና ምርምር ዓለም አቀፍ ማዕከል (አይሲኤአርዲኤ)። HTTPS://HDL.HANDLE.NET/20.500.11766/12542

ኢሳያስ ሙላቱ፣ ጄን ዋማቱ (23/12/2019)። የኢትዮጵያ ማይክሮ ፋይናንስ የመሬት ገጽታ ሪፖርት፣ የዘመነ ኦክቶበር 2020። HTTPS://HDL.HANDLE.NET/20.500.11766/10765

ክፍለ ጊዜ 5. በጎችን ማድለብ እንደ ንግድ

ክፍል 5.2፡ የፋይናንሺያል ትምህርት

የፋይናንሺያል እውቀት ግለሰቦች ስለ ገንዘብ ነክ ጉዳዮች በመረጃ ላይ የተመሰረተ እና ውጤታማ ውሳኔ እንዲያደርጉ የሚያስችላቸውን የክህሎት እና የእውቀት ስብስቦችን ያመለክታል። የፋይናንስ ምላሽ፣ እውቀት፣ ችሎታ፣ አመለካከት ጥምረት ነው፤ እና በመረጃ የተደገፈ የፋይናንስ ውሳኔዎችን ለማድረግ እና በመጨረሻም የግለሰብ ኢኮኖሚያዊ ደህንነትን ለማሳካት የሚያስፈልጉ ባህሪያት ናቸው።

በአጠቃላይ የእውቀት (ኮግኒቲቭ) ግንዛቤ ወደ ፋይናንስ ሞጁሎች እና ችሎታዎች እንደ በጀት ማውጣት፣ ቁጠባ፣ ኢንቨስት ማድረግ፣ መበደር፣ ቀረጥ፤ እና የግል ፋይናንስ አስተዳደር፤ የፋይናንሺያል ዕውቀት ተብሎ ይጠራል።

የእነዚህ ክህሎቶች እጥረት የፋይናንስ እውቀት እጥረት በመባል ይታወቃል።

የቅድመ እና ድህረ ግምገማ ጥያቄዎች:

1. የፋይናንስ እውቀት አስፈላጊ ነው?

2. በጀት ማውጣት ምንድነው እና ምንን ይጨምራል?

3. የራስዎን የፋይናንስ እቅድ ለማውጣት ምን ማድረግ ይችላሉ?

4. በበጀት አመዳደብ የገንዘብ አያያዝን ለማሻሻል አማራጮች ምንድናቸው?

5. የቁጠባ አማራጮችን ከመወሰንዎ በፊት ምን ግምት ውስጥ ማስገባት አለብዎት?

6. ብድር ለመውሰድ ምክንያቶች ወይም ጊዜዎች ምንድናቸው?

7. ለምን ኢንቨስት ማድረግ አለብን?

8. ኢንቨስት ለማድረግ በጣም ጥሩው ጊዜ መቼ ነው?

9. በአከባቢዎ እና በንግድዎ ውስጥ የአደጋ ምንጮች ምንድናቸው?

10. ኢንሹራንስ ምንድነው እና ለምን አስፈላጊ ነው?

11. ለምን እና እንዴት የፋይናንስ አስተዳደርን እንደ የህብረት ሥራ ማህበር አባልነት ይለማመዳሉ

በግ የሚያደልቡ ገበሬዎች በግለሰብም ሆነ በሕብረት ሥራ ማኅበራት የፋይናንስ እውቀት ያስፈልጋቸዋል ምክንያቱም:-

- ✓ እንደ የግል ወይም የድርጅት የፋይናንስ አስተዳደር፣ በጀት ማውጣት፣ ቁጠባ፣ ኢንቬስትመንት እና ብድር መስጠት ያሉ ቁልፍ የፋይናንስ አገልግሎቶችን እና ምርቶችን ይረዱ፤
- ✓ ስለ ፋይናንስ አገልግሎቶች ያላውን አስተሳሰብ ይቀይሩ
- ✓ ከፋይናንሺያል አገልግሎቶች ማግኘት እና ጥቅም ማግኘት
- ✓ የግል ፋይናንስ ጉዳዮችን ግንዛቤን የሚያጎለብት እውቀት እና ክህሎት ይኑርህ እና የግል ፋይናንስን ለማስተዳደር የፋይናንሺያል እውቀትን የመተግበር ችሎታ።

ክፍለ ጊዜ 5. በጎችን ማድለብ እንደ ንግድ

✓ የፋይናንስ ግቦችን በማውጣት
የወደፊት ወጪዎችን እና
ኢንቨስትመንቶችን ይተነብዩ

መሠረታዊ ፍላጎቶች	መሻቶች
▪ የገንዘብ ጉዳዮችን ለመመልከት እና የፋይናንስ አገልግሎቶችን ለማግኘት እምቢ ማለት ▪ የፋይናንስ አገልግሎቶች እና ባለሙያዎች አለመተማመን ▪ በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ መኖር ▪ በመበደር ላይ የፋይናንሺያል ግብ ጋር የተገናኘ አይደለም እና በአጠቃላይ ለአደጋ ጊዜ ብድር ይሰጣል ▪ ትክክለኛውን ኢንቨስትመንት መምረጥ አይቻልም ▪ ሂደቶችን፣ ገቢዎችን እና ወጪዎችን መከታተል አለመቻል እና የወደፊቱን መተንበይ አይቻልም	▪ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በራስ መተማመን ይድረሱ ▪ የፋይናንስ አገልግሎቶችን በተመለከተ ከባለሙያዎች ምክር እና ምክር ይጠይቁ ▪ የወጪ እና የበጀት እቅድ አውጡ እና ስራውን ለማስተዳደር ያቅዱት። ▪ ግልጽ ዓላማዎች ያለው የቁጠባ እቅድ ይኑርዎት እና የአደጋ ጊዜ ቁጠባ ፈንድ ይጠብቃል። ▪ ትክክለኛውን ኢንቨስትመንት ይምረጡ ▪ እድገትን፣ ገቢዎችን እና ወጪዎችን ለመከታተል እና ስለወደፊቱ ጊዜ ለመተንበይ መዝገቦችን ይያዙ

✓ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ስለ ወጪ ማውጣት እና ስለማዳን እና ኢንቬስት ለማድረግ ወይም ንግዳቸውን ለማስቀጠል እና አፈፃፀሙን ለማሻሻል ጥሩ የፋይናንስ ውሳኔዎችን ያድርጉ።

✓ ገቢያቸውን እና ወጪያቸውን ለመቆጣጠር የፋይናንሺያል ግብይቶች ትክክለኛ መዝገቦችን ያስቀምጡ።

✓ በቤተሰባቸው እና በንግድ ስራዎቻቸው የዕለት ተዕለት የፋይናንስ ደህንነት ላይ ተጽእኖ ሊያሳድሩ ለሚችሉ ለውጦች እና አደጋዎች በብቃት ምላሽ ይስጡ።

ተጨማሪ ንባብ፡ ለአነስተኛ በግ አርሶአደሮች የገንዘብ እውቀት:
https://hdl.handle.net/20.500.11766/12629

ክፍለ ጊዜ 5. በጎችን ማድለብ እንደ ንግድ

ክፍል 5.3፡ ግብይት እና የጋራ ግብይት ቅድመ እና ድህረ ግምገማ ጥያቄዎች:

1. ግብይት ምንድነው?
2. የጋራ-ግብይት ምንድነው?
3. አርሶ አደሮችን በገበያ ላይ ተወዳዳሪ ለማድረግ የጋራ ተግባራት አስፈላጊነት ግለጽ።

የግብይት እና የገበያ መመሪያ፡ ገበያ፣ በአካል ወይም በፅንሰ-ሃሳቡ፤ ልውውጥ የሚካሄድበት ቦታ ነው። ግብይት፤ በሸቀጦች እና አገልግሎቶች ፍሰት ውስጥ የተካተቱት ሁሉም የንግድ እንቅስቃሴዎች አፈፃፀም ከመጀመሪያው ምርት እስከ መጨረሻው ሸማች ድረስ ያካተተ ነው። ግብይት ዕቃዎችን በቦታ፣ በጊዜ እና በቅርጽ ከአምራቾች ወደ ሸማቾች መቀየርን ያካትታል። እነዚህ የለውጥ ሂደቶች፤ ቀልጣፋ መሆን አለበት፣ ማለትም፣ ከሸማቾች ምርጫዎች እና ገቢዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ በዝቅተኛ ወጪ የተጠናቀቀ ነው።

ለስኬታማ ግብይት፣ የሚከተለውን ልብ ማለት አስፈላጊ ነው:

- ✓ በጎቻችሁ በሚፈለጉበት ሰሞን ለገበያ ያቅርቡ።
- ✓ ተገቢውን የገበያ መረጃ ሰብስቡ።
- ✓ ከነጋዴዎች ጋር ጥሩ ግንኙነት መፍጠር። በተቻለ መጠን ከደላሎች መራቅ እና የሰባ በግ በቀጥታ ለተጠቃሚዎች ማቅረብ ይመረጣል።
- ✓ የመደራደር አቅምን ለማሻሻል እና ከፍተኛ ዋጋ ለማግኘት የጋራ ግብይትን ይለማመዱ።

የጋራ ግብይት፡ ገበሬዎች በጎቻቸውን ወደ ገበያ በማምጣት በደላሎችና በነጋዴዎች ላይ ድርድር ያደርጋሉ። ብዙውን ጊዜ ስለ ድቡልቡ በግ የገበያ መረጃ ይጎድላቸዋል እና ለገንዘብ ፍላጎታቸው በችግር ሽያጭ ላይ ይሳተፋሉ። ግብይቶቻቸውን ለሌላ ጊዜ ለማስተላለፍ ትንሽ ወይም ምንም አማራጭ ሳይኖራቸው ወዲያውኑ ይሸጣሉ።

አርሶ አደሩ በገበያው ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲወዳደር ከሚረዱት ውስጥ አንዱ የጋራ ተግባር ተለይቷል። የጋራ ተግባር የሰዎች ስብስብ ተሳትፎን ይጠይቃል, በቡድኑ ውስጥ የጋራ ፍላጎቶች፤ እና በበጎ ፈቃደኝነት ለጋራ ጥቅም ቁርጠኝነትን ያካትታል. የጋራ ተግባር፤ ግለሰቦች ለግለሰቦች በጣም ውድ ሊሆኑ የሚችሉ እቃዎችን እና አገልግሎቶችን በብቃት እንዲያገኙ እና እንዲጠቀሙ የሚያስችል ስትራቴጂ ነው። ከግለሰብ ግብይት ጋር ሲነጻጸር, የጋራ አቀራረብ፤ ለገበሬዎች ብዙ ጥቅሞች ስላሉት ይመከራል፣ ከእነዚህም መካከል-

- ✓ የጋራ ድርድር እና የተሻሻለ ዋጋ።
- ✓ የተሻሻለ እውቀት እና መረጃ መጋራት።
- ✓ ከገዢዎች ጋር መገናኘትን ቀላል ማድረግ
- ✓ ቀጣይነት ያለው የዋጋ መሻሻል።
- ✓ የተሻለ ግንኙነት እና መረጃ።

ክፍለ ጊዜ 5. በጎችን ማድለብ እንደ ንግድ

በኢትዮጵያ ውስጥ ለግብርና ግብይት በጣም የተለመዱ የጋራ ተግባራት፤ የገበያ ወይም የአገልግሎት ህብረት ስራ ማህበራት ናቸው። የበግ ማድለብ ህብረት ስራ ማህበራት፤ በአባሎቻቸው የምረባው የሰባ በግ ለገበያ ለማቅረብ ተዘጋጅተዋል። እነዚህ የህብረት ሥራ ማህበራት፤ በወጣቶች አምራቾች መካከል በደጋማ አካባቢዎች የተለመዱ ናቸው. የአገልግሎት ህብረት ስራ ማህበራት፤ የግለሰብ አባላትን የግብይት ወጪ ለመቀነስ ለግብይት ግብዓቶች እና ውጤቶች ዓላማ ብቻ የተቋቋሙ ናቸው። የግብይት ህብረት ስራ ማህበራት ከሚከተሉት ተግባራት ውስጥ በማንኛቸውም ይሳተፋሉ።

- ✓ የተመረጡ የተሻሻሉ የመኖ ሰብሎች ወይም የመትከያ ቁሳቁስ፣ የእንስሳት መድኃኒቶች፣ መሣሪያዎች እና መሳሪያዎች፣ የእንስሳት መኖ እና ተጨማሪዎች አቅርቦት።
- ✓ በዱቤ ዕቅዶች - በጥሬ ገንዘብ ወይም በሸቀጦች ላይ የተመሠረተ የገንዘብ አቅርቦት
- ✓ በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ገበያዎች ግብይት።

የትብብር ሥራን የሚወስኑ ዋና ዋና ነገሮች፤ በአራት ምድቦች ሊከፈል ይችላል። እነዚህ የቡድን አባላት ባህሪያት፣ ተቋማዊ ዝግጅቶች፣ ምርቶች እና ገበያዎች የጋራ እርምጃ እና የጋራ ድርጊት የሚሠራበት ውጫዊ አካባቢ የተነደፈ ነው።

የውይይት ነጥቦች

- ✓ የድልብ በግ በሚሸጡበት ጊዜ በገበያዎች ውስጥ ምን ችግሮች ያጋጥሙዎታል?
- ✓ በአካባቢያችሁ ያሉ የጋራ ድርጊቶች ድክመቶች እና ጥንካሬዎች ምንድናቸው?
- ✓ የህብረት ሥራ ማህበራት ለአባሎቻቸው የበለጠ ጠቃሚ እንዲሆኑ መለወጥ ያለባቸው ምን ይመስላችኋል?
- ✓ በግለሰብ እና በቡድን ፍላጎቶች መካከል ያለውን ልዩነት እና በጋራ ተግባር ላይ ያለውን ተጽእኖ ያብራሩ።
- ✓ እርስዎ አባል የሆኑባቸው የህብረት ሥራ ማህበራት ወይም ቡድኖች ሁሉንም ደንቦች እና ደንቦች ተረድተዋል።
- ✓ የጋራ ተግባራትን ውጤታማ ለማድረግ የመንግስት ኤጀንሲዎች ድጋፍ ጠቃሚ ይሆናል ብለው ያስባሉ? ለምን?
- ✓ የጋራ ቡድን አባላት እኩል ኃላፊነት እንዲሰማቸው እና ከነሱ ይጠበቃል በሚለው አስተዋጽኦ ለማድረግ እንዲችሉ ምን መደረግ ያለበትይ ይመስላችኋል?
- ✓ በእርስዎ አስተያየት የጋራ ድርጊቶችን ዘላቂነት የሚወስነው በጣም አስፈላጊው ነገር ላይ ምን ማድረግ አለብዎት? ለምን?

ክፍለ ጊዜ 5. በጎችን ማድለብ እንደ ንግድ

ተጨማሪ ንባብ፡- ካስዬ፣ ጊ.ቲ አስናቀ፣ ወ.ኃይሌ፣ አ. ጌታቸው፣ ዋማቱ ጄ. 2020 የጋራ ተግባር ለግብርና ግብይት- የሥልጠና መመሪያ። ዓለም አቀፍ የግብርና ምርምር በደረቅ አካባቢዎች (አይሲኤአርዲኤ)፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፡ አይሲኤአርዲኤ።

https://hdl.handle.net/20.500.11766/12629



© ቦንጋ ፡ የቡታ ጋኒቲ በግ ማድለብ እና የተሻሻለ የግጦሽ ዘር ማባዛት ትብብር።

ክፍለ ጊዜ 5. በጎችን ማድለብ እንደ ንግድ



© ቢኤአርሲ/ሙሉቀን ዘለቀ፡ የሻያ ሴቶች ህብረት ስራ ማህበር ቦንጋ



© ቦንጋ ኤአርሲ፡ የቡታ ጋኒቲ በግ ማድለብ እና የተሻሻለ የግጦሽ ዘር ማባዛት ትብብር።

ክፍለ ጊዜ 5. በጎችን ማድለብ እንደ ንግድ

ተጨማሪ ንባብ

ዋማቱ፣ ጄ. 2021. ወጣቶችን በገበያ ላይ ያተኮረ በግ ማድለብ አራማጆች ላይ ያነጣጠረ የዳበረ አካሄድ። አይሲኤአርዲኤ፡ ፓኖራማ መፍትሄዎች ፖርታል https://panorama. solutions/en/solution/scaling-approach-targetingyouth-promoters-marketoriented-sheep-fattening
ዋማቱ፣ ጄ እና ኤፍሬም፣ N. 2020. በግ ማድለብ፤ በኢትዮጵያ ለወጣቶች የስራ ፈጠራ እድል እየፈጠረ ነው። የብሎግ ልጥፍ
በ https://livestock.cgiar. org/news/sheep-fatteningcreating-entrepreneurialopportunities-youth-ethiopia

ዘመዱ፣ ኤል.፣ ካሴ፣ ጂ.፣ ሃይሌ፣ አ.፣ ዋማቱ፣ ጄ.፣ ሂላሊ፣ ኤም.ኢ.ዲ እና ሪሸኮውስኪ፣ ቢ. 2018፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ አነስተኛ የከብት እሴት ሰንሰለቶች ላይ የተመረጡ ምርጥ ቤት ጣልቃገብነቶች የገንዘብ አዋጭነት። ኢትዮጵያ፡ አይሲኤአርዲኤ
https://repo.mel.cgiar.org/handle/20.500.11766/9566

የስምምነት መግለጫ፡- “ስም፣ የንግድ ርዕስ፣ ኢሜል፣ ስልኮች፣ ምስሎች እና የጂፒኤስ ነጥቦችን ጨምሮ የግል መረጃ በውሂቡ ርዕሰ ክፍል በጽሁፍ ወይም በቃላት ተፈቅዶላቸዋል። ሁሉም ከ16 አመት በታች ያሉ ታዳጊዎች ፎቶግራፎች የተነሱት ከወላጆች የቃል ስምምነት ነው” ጄ. ዋማቱ





Sheep Fattening Cooperatives

Empowering Youth in Ethiopia

"ወጣቶች እና ሰቶች በበግ ድለባ ማህበር ተደራጅተን በስልጠና ማኑዋል የተዘረዘሩት ሳይንሳዊ መርሆዎችን በአግባቡ በመተግበራችን በየጊዜው የኢኮኖሚ አቅማችንን ማሳደግ ችለናል"

ወ/ሮ አምለሰች ኃይለማርያም በካፋ ዞን አዲዮ ወረዳ የሴቶች ማህበር ስብሰቢ

CGIAR RESEARCH PROGRAM ON Livestock

TAAT Technologies for African Agricultural Transformation

SARI 2001

ABARI

ISBN 978-99990-975-0-5

9 789999 097505 >